ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991

# መለዕክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር ሰባት ግንቦት 2012 ዓ/ም

# የዚህ ዘመን አርበኞች!

ሰቆቃዎ ክረምት

ተጠንቀቅ!

ህገ ወጥ እስራትና አሁናዊ እውነታዎች



# ርእሰ አንቀጽ

ኢሰመጉ

## ፖለቲከኛ ልቡን ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?

ለሁለት ዓመታት ያህል በሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ረገድ መሻሻል ስለማሳየቷ በአገር በቀልና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተማጓች ተቋማት ሲመሰከርላት የቆየችው ኢትዮጵያ ሰሞኑን ስሟ ዳግም በአሉታዊ መልኩ ሲነሣ ሰንብቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ‹‹አምነስቲ ኢንተርናሽናል››

በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች በሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ምርመራ አከናውኖ ይፋ ያደረገው መግለጫ ነው፡፡ የሪፖርቱን ይፋ መሆን ተከትሎ የሁለቱ ክልሎች ባለ ሥልጣናት ጠንካራ የማስተባበያ መግለጫዎች አውጥተዋል፡፡

ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግም በጉዳዩ ላይ ምርመራ በማድረግ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ አካላት ለፍርድ እንዲቀርቡ እንደሚያደርግ አስታውቋል፡፡

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ሰፋ ባለ መልኩ ዝርዝር መግለጫውን ይፋ ከማድረጉ ሳምንታት ቀደም ብሎ ኢሰመጉ ግንቦት 7 ቀን 2012ዓ.ም ‹‹በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ያለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ በሆነ ደረጃ ላይ ይገኛል!›› በሚል አርእስት ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ በተለይም

በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች በመንግሥት ኃይሎችና ታጣቂ ቡድኖች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እየተፈጸሙ መሆኑን አሳስቧል፡፡

ነገር ግን፣ በክልሎቹ መንግሥታት በኩል የተወሰደው አማራጭ ‹‹ከለውጡ›› በፊት እንታዘብ የነበረውን የመንግሥት ምላሽ በሚያስታውስ መልኩ ዋናውን ፍሬ ነገር ሳይሆን ‹‹መልዕክተኛውን›› ዒላማ ባደረገ መልኩ የሪፖርት አቅራቢውን አካል ተዐማኒነት ጥያቄ ውስጥ ለመክተት የሚሞክር ምላሽ መስጠት ሆኖ ተስተውሏል፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ ይደረግ የነበረው የሰብዓዊ መብቶች ተቋማትን መግለጫዎች ሙሉ በሙሉ ውድቅ የማድረግ አካሄድ ሥልቱ ተለውጦ ተፈጽመዋል ለሚባሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሌሎች አካላትን ተጠያቂ ለማድረግ፣ ‹በፖሊቲካ ዐውድ› ትንታኔ ነገሩን አድበስብሶ ለማለፍ ሲሞከር ተስተውሏል፡፡

የሰብዓዊ መብቶችን በማክበር፣ በማስከበርና መብቶች የሚከበሩበትን ሁኔታ በማሟላት ረገድ ዋነኛ ግዴታ የተጣለበት መንግሥት በመሆኑ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ኃላፊነቱን በታጣቂ ቡድኖች ላይ ብቻ አድርጎ ለማለፍ መሞከር ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

ታጣቂ ኃይሎችንም ለመቆጣጠር የሚወሰደው እርምጃ ሰላማዊ ዜጎችን ለተጨማሪ ጥቃት የማያጋልጥ መሆን አለበት፤ የጅምላ ቅጣት በሚመስል መልክ መፈጸም የለበትም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንም የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል ታስቦ ከወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ አፈጻጸም ጋር በተገናኘ የተስተዋሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዲታረሙ ለመንግሥት ምክረ ሐሳብ በማቅረቡ በከፍተኛ የሥልጣን እርከን ላይ የሚገኙ ሹማምት በኮሚሽኑ ላይ ውግዘት ሲያሰሙ ሰንብተዋል፡፡

በኢትዮጵያ አስከፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ይፈጸሙ በነበረበት ጊዜም በሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች ‹‹ኮሚሽኑ በሰብዓዊ መብት ስም በመንግሥት ላይ አላስፈላጊ ተጽእኖ መፍጠር አይገባውም!›› የሚል ኃይለ ቃል ሲሰነዝሩ መስማታችን ነው ‹‹ፖለቲከኛ ልቡን ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?›› ብለን እንድንጠይቅ ያስገደደን፡፡

በመሠረቱ እንደ ኢሰመጉ ባሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ አገር በቀል የሰብዓዊ መብቶች ተከላካዮች፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንን በመሰሉ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማትና አምነስቲ ኢንተርናሽናልን በመሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ይፋ የሚሆኑ መግለጫዎች ዋና

ዓላማ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመከላከልና ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መርሖዎች የሚተገበሩበት ሥርዓት ሊፈጠሩ የሚችሉበትን መንገድ ማመላከት ነው፡፡

በማስረጃ ተደግፈው የሚቀርቡ ሪፖርቶችንና ምክረ ሐሳቦችን አለመቀበል፣ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማትን ማውገዝና በእነርሱ ላይ ጫና ለማሳደር መሞከር የኋልዮሽ ጉዞ እንዳንጀምር ማስጠንቀቂያ ደወል ነው፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋማት ለሚያወጧቸው መግለጫዎች መንግሥታት የሚሰጧቸው ምላሾች ብዙውን ጊዜ የፖሊቲካዊ ባሕልንና ርእዮተ ዓለምን የሚያንጸባርቁ በመሆናቸው ሰሞኑን ያስተዋልናቸውን አዝማሚያዎች በጥንቃቄ መመልከት ይኖርብናል፡፡

ስለሆነም፣ እነዚህ ተቋማት መግለጫ ይፋ ባደረጉ ቁጥር የማስተባበል ዘመቻ ከመክፈት ይልቅ በ ‹‹ሊሆን ይችላል›› መንፈስ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ነው ከመንግሥት

የሚጠበቀው፡፡



## መልእክተ ኢሰመጉ


### አሳታሚ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

### የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች

ብንያም አባተ
ዳን ይርጋ
ሱራፍኤል ግርማ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም



### የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢሜል= info@ehrco.org


ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

# ሰዋዊ

# ሰቆቃው ክረምት!

በሱራፍኤል ግርማ

ትኩረታችን ሁሉ በኮሮና ቫይረስ ላይ ሆኖ በሰነበተበት በዚህ ሰሞን በአዲስ አበባ ከተማ ዳርቻዎች መጠነ ሰፊ የሆነ ቤት የማፍረስ ዘመቻ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ ጉዳዩም ‹‹የበሽታ ወረርሽኝ በተከሰተበትና ክረምት በተቃረበበት በዚህ ወቅት እንዴት ዜጎች ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው ጎዳና ላይ እንዲወድቁ ይደረጋል?››

የሚል ጥያቄ አስነሥቷል፡፡ ቤት የማፍረስ ዘመቻዎች ከተከናወኑባቸው ክፍለ ከተሞች መካከል የአንዳንዶቹ አመራሮችም ለዚህ ጥያቄ ‹‹የፈረሱት ሕጋዊ መኖሪያ ቤቶች ሳይሆኑ በወረራ በተያዘ መሬት ላይ የተቀለሱ ሕገ ወጥ የጨረቃ ቤቶች ናቸው፡፡›› የሚል መልስ ሲሰጡ ተደምጠዋል፡፡

በዚህ ጽሑፍ፣ ሕገ ወጥ የጨረቃ ቤቶች ግንባታ በከተማይቱ ውስጥ ለምን እየተስፋፋ እንደመጣ ጥያቄ በማንሣት ጉዳዩን ከሰብዓዊ መብት አንፃር ለመመልከትና ለተጨማሪ ውይይት መንገድ ለመክፈት እንሞክራለን፡፡ ‹‹በአዲስ አበባ ሕገ ወጥ የቤቶች ግንባታ ለምን ተስፋፋ?›› ለሚለው ጥያቄ ሊቀርቡ ከሚችሉ በርካታ ምላሾች መካከል በእኔ ዕምነት በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀመጠው በ ‹‹ሕጋዊው›› መንገድ የቤት ባለቤት መሆን ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሕልም ደረጃ የተወሰነ መሆኑ ነው፡፡

የሥራ አጥ ዜጎች ቁጥር እየናረ ባለበት፣ የገንዘብ የመግዛት ዐቅም እያሽቆለቆለ በሆነበት፣ ከመሠረታዊ ፍጆታ ተርፎ ለቁጠባ የሚበቃ ምንዳ የሚያገኙ ተቀጣሪዎች እጅግ በጣም ጥቂት ሆነው በሚገኙበት የአገራችን ነባራዊ እውነታ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ኖሯቸው መኖሪያ ቤት መገንባት አሊያም መግዛት የሚችሉት በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ በመንግሥታዊው ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ አሊያም በውጭ አገራት የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሕግ አካል ከሆኑ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መካከል አንዱ የሆነው የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ ዐሥራ አንድ እንዲህ ይላል፡- ‹‹የቃል ኪዳኑ ተዋዋይ አገራት ማንኛውም ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መኖሪያ ቤትን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ በሆነ የኑሮ ደረጃ ለመኖርና ኑሮውንም በየጊዜው ለማሻሻል መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ፡፡ አባል አገሮቹ

በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ ትብብርን አስፈላጊነት ተገንዝበው ይህን መብት ሙሉ ለሙሉ በሥራ ለመተርጎም ተገቢውን ርምጃ ይወስዳሉ፡፡››

በዚሁ መንፈስ የተቃኘ በሚመስል መልኩ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ መርሐ ግብር ከተጀመረ የአንድ ጎረምሳ ዕድሜ ያህል ዘመን ተቆጥሯል፡፡ ዳሩ ግን ብዙኃኑን የከተማዋን ነዋሪዎች ለመጥቀም ታስበው የተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በነቀዘ ብሔር ተኮር ፖሊቲካዊ አሠራር ምክንያት የጥቂት ባለጠጎች ንብረት ሲሆኑ ታዝበናል፡፡

በኢትዮጵያ እኩልና ከአድልዎ ነጻ በሆነ መልኩ ለኑሮ በቂ የሆነ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ሊከበር ባለመቻሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ለሕይወታቸውና ለጤንነታቸው አሥጊ በሆኑ፣ በጣም በተጣበቡና ‹‹ቤት›› ተብለው ሊጠሩ በማይችሉ ቅልሶች ውስጥ ለመኖር ተገድደዋል፡፡

## ቤት ሲባል . . .

በተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤት ለኑሮ በቂ የሆነ ቤት የማግኘት መብትን በተመለከተ ባሳተመው አንድ ሠነድ ላይ እንደተገለጸው ‹‹መኖሪያ ቤት›› ማለት ከአራት ግድግዳና ጣራ በላይ ሌሎች ነገሮችንም አሟልቶ የያዘ መሆን አለበት፡፡

እነዚህ መሠረታዊ አቅርቦቶች የቤት ግንባታውን ያህል አስፈላጊ ናቸው፡፡ በተ.መ.ድ መሥፈርት አንድ ቤት ‹‹መኖሪያ ቤት›› ሊባል የሚችለው ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን ሲያሟላ ነው፡፡

- ንጹሕ የመጠጥ ውኃና በቂ መጸዳጃ እንዲሁም ተገቢ የሆነ የቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት፣ ለብርሃንና ለምግብ ማብሰያ በቂ የኃይል አቅርቦት ሊሟሉ ይገባል፡፡

- ቤት ለመግዛት፣ ለመገንባት ወይም ለመከራየት የሚወጣው ገንዘብ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ነዋሪዎችን ለድህነት የሚዳርግ

# ሰዋዊ

ከሆነ፣ ጠባብ ከመሆኑ የተነሣ ለኑሮ ተስማሚ ካልሆነ፣ ነዋሪዎቹን ለቅዝቃዜ፣ ለሙቀት፣ ለዝናብ፣ ለነፋስ ወይም ለሌሎች የጤና ሥጋቶች

የሚያጋልጥ ከሆነ . . . ከሥራ ቦታ፣ ከት/ቤት፣ ከጤና ተቋማት ወዘተ. የራቀና በተበከሉ ወይም ለኑሮ አደገኛ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኝ ከሆነ በቂ የመኖሪያ ቤት አለ ለማለት አይቻልም፡፡

እንግዲህ ከላይ በጥቂቱ በተዘረዘሩት መሥፈርቶች መሠረት እያንዳንዱ መንደር ቢፈተሽ ስንቶች ናቸው በእውነቱ ‹‹ቤት ውስጥ›› የሚኖሩ ሆነው የሚገኙ? እርግጥ ነው፣ ‹‹በቂ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት›› ሲባል መንግሥት ለሁሉም ዜጎች ቤት ገንብቶ እንዲያቀርብ ግዴታ አለበት ማለት አይደለም፡፡

ከዚያ ይልቅ ከመንግሥት የሚጠበቀው ቤት አልባነትን ለማስወገድ፣ ዜጎች ከግል ይዞታቸው ወይም ተከራይተው ከሚኖሩበት ቤት በግድ እንዳይፈናቀሉ ለመከላከል እንዲሁም አድሎአዊ አሠራርን ለማስወገድ የሚያስችሉ ሕጋዊና ፖሊቲካዊ ርምጃዎችን መውሰድ ነው፡፡

ሰብዓዊ መብቶች የማይነጣጠሉ፣ የማይሸራረፉና እርስ በእርሳቸው የተቆራኙ በመሆናቸው ለኑሮ በቂ የሆነ ቤት የማግኘት መብት ሲጣስ ሌሎች በርካታ ሰብዓዊ መብቶችም እንዲጣሱ ምክንያት ይሆናል፡፡ ለኑሮ በቂ የሆነ ቤት የማግኘት መብት የመረጡትን መተዳደሪያ ለመሥራት መብት፣ ለ የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት፣ ለመምረጥና መመረጥ መብት እንዲሁም የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት መብት ቅድመ ሁኔታ ሊሆን ይችላል፡፡

ለምሳሌ፣ የአንድ አካባቢ ነዋሪነት መታወቂያ ወረቀት የሌላቸው ዜጎች በምርጫ ወቅት ተወዳዳሪ ሆነው ለመቅረብ ይቅርና በመራጭነት እንኳ ድምፃቸውን ለመስጠት አይችሉም፡፡

## መፍትሔው . . .

የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት የመንግሥት ብቻ መሆኑ በተደነገገበት የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንጽ 40(3) መሬት የማይሸጥና የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ ተገልጻ□ል፡፡

በተግባር የምናየው ግን መሬት ከምንም ነገር በላይ እጅግ በናረ ትልቅ ዋጋ የሚሸጥ ውድ ሸቀጥ መሆኑን ነው፡፡ ዋነኛው የመሬት አቅራቢና ነጋዴ መንግሥት በመሆኑ ለኑሮ በቂ የሆነ ቤት የማግኘት መብት ይከበር ዘንድ መሠረታዊ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው የመሬት አቅርቦት አስከፊ አድሎአዊ አሠራር የሚንጸባረቅበት የብሔር ተኮር ፖሊቲካ ማስፈጸሚያ ሆኗል፡፡

በዚህም ምክንያት በብሔር ማንነታቸው ወይም በፖሊቲካ ዐቋማቸው ተመዝነው ‹‹ባለ ጊዜ›› ያልሆኑ ወይም በባለ ሥልጣኖች የሚጠየቁትን ጉቦ መስጠት የማይችሉ ዜጎች የመኖሪያ ቤት ባለ ንብረት ለመሆን አይችሉም፡፡

የከተማ ውበት ከማጉደፍ በላይ ለኑሮ ፈጽሞ ተስማሚ ያልሆኑና ለአደገኛ ወንጀሎች መፈልፈያ ሊሆኑ የሚችሉ ‹‹የጨረቃ ቤቶች›› ግንባታና ጎስቋላ መንደሮች መስፋፋት የሚገታው መንግሥት በብሔርና በፖሊቲካ ድርጅት አባልነት ላይ ተመሥርቶ የሚፈጸም አድሎአዊ አሠራርን በማስወገድ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ የገቢ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች በእውነት የቤት ባለቤቶች ሊሆኑ የሚችሉባቸውን የልማት ዕቅዶች በመቀየስ፣ ለቤት ግንባታ የሚሆን የብድርና የቦታ አቅርቦት ሲያመቻች ብቻ ነው፡፡

ክረምት በመጣ ቁጥር መጠለያ አልባ ሆነው በየጎዳናው የወደቁ ወገኖቻችንን ሰቆቃ ማየት የምናበቃውም የዚያኔ ነው፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ከፍ ያለ ስም!!!

ኮሮና



## የዚህ ዘመን አርበኞች!

ገላውዲዮስ ግሩም

ዓለም በዚህ ክፉ በሽታ ከተመታች ጀምሮ አያሌ ነገሮችን አስተውለናል። የሰው ልጆች መተማመኛ እሚሆን እሚታደጋቸው አጥተው በራቸውን ዘግተዋል። መቼም ይህ ሁኔታ በቅርብ ጊዜ ተከስቶ የአልምን ህዝብ እኩል መድረሻ ማሳጣቱ ብዙ ነገሮችን ሰርቻለሁ ለሚለው የሰው ልጅ አእምሮ ብዙ እንደሚቀረው ወለል አድርጎ እሚያሳይ ነው። የስልጣኔ ቁንጮ ብለን የምናሞካሻቸው ሀገራትም አስቀድመው መፍትሄውን ከመፈለግ ይልቅ እጃቸውን አሻግረው እየዘረጉ ለ ቫይረሱ መንስኤ ናቸው ብለው ያሰቧቸውን ሀገራት እና ተቋማት ሲኮንኑ አስተውለናል።

ወረርሽኙ የቀየረው እና የገለጠው ሁለተናዊ ለውጥ በእጅጉ እሚስተዋል ነው። ይህን ከፉ ወቅት በመጠቀም እማይሞላ ስግብግብነትን ለማስታገስ ከተሯሯጡት ግለሰቦች እስከ ራሳቸውን መስዋእት አድርገው ፊት ለፊት እስከተጋፈጡት ድረስ እንድናይ ሆነናል።

የከፉዎችን ላዛሬ ትተን በዚህ አስቸጋሪ ወቅት በሀገራችን ያስተዋልናቸውን የመልካምነት አምባሳደሮች እና የዚህ ዘመን አርበኞችን በዛሬው የ ከፍ ያለ ስም አምድ እናመሰግናለን ልንላቸው ወደናል። አብራቹህን ቆዩ

የ ኮሮና ቫይረስ ሀገራችን መግባቱ ከተረጋገጠበት ቀን አንስቶ ማህበረሰቡ አነሰም በዛም በደግነት እንቅስቃሴ ሲሳተፍ ቆይቷል። በእርግጥ በ እኛ ሀገር ሰዎች ለሰዎች መቆም እና መልካም ማድረግ የኖርንበት በመሆኑ ብዙም ላይገርም ይችላል። ነገር ግን በእንደዚህ አይነት ወቅቶች በተለየ ሁኔታ ሰዎች በደግነት የሚያደርጓቸው መልካም ነገሮች የማህበሰቡን መነቃቃት የሚያመጣ እና ከልዩነቶቻችን በላይ አብሮነታችን እንደሚገዝፍ  እሚያሳዩ ናቸው።

በማህበረስብ ግንባታ ውስጥ ከሚጠበቁ ነገሮች ዋነኛው ማህበረሰቡ ዋጋ ከፍሎ ያስተማራቸው ምሁራን ተመልሰው የወጡበትን ማህበረሰብ እንዲያገለግሉ ነው። ታዲያ በዚህ ወረርሽኝ ወቅት ማህበረሰባቸው ይጣለባቸውን ከፍተኛ ሀላፊነት በሚያስደንቅ ብቃት እና መስዋእትነት እየከፈሉ የሚገኙ አካላት ብዙ ናቸው ። ከነዚህም መካከል ይህ ከፉ ጊዜ ሲያልፍ በአርበኝነት የምናከብራቸው የህክምና ባለሙያዎች ሂዎታቸውን ለዎገኖቻቸው ለግሰው በየቀኑ ከሞት ጋር እየተናነቁ በከፍተኛ ቁርጠኝነት እያገለገሉን ይኝያሉ።

የተሟላ ህክምና ቅንጦት በሆነባት በእኛ ሀገር እንኳን እንደዚህ አይነት ከባድ ፈተና ገጥሞት ቀድሞውንም የህክምና ባለሙያዎቻችን በከፍተኛ የ ህክምና ቁሳቁስ እና ጥንቃቄ እጥረት ሀገራቸውን ሲያገለግሉ እንደቆዩ ይታዎቃል።

ይሁን እንጂ በዚህ ዎቅት ባልተሟላ አቅርቦት ያለምንም እረፍት ይህን ከፉ ጠላት ድል ሊነሱት ታጥቀው እየሰሩ ነው። በዚህም ጊዜ የማይሽረው ወርቃማ ታሪክን እየጻፉ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የህክምና ባለሙያዎች በዚህ ወቅት ከ ኮሮና ጋር እየተናነቁ እስከወዲያኛው በሚያኮራ ጀግንነት ሽኝተናቸዋል። በሀገራችን እንኳ እስካሁን ድረስ ከ 90 የሚበልጡ ሰዎች በ ቫይረሱ ተይዘዋል። ታዲያ እነዚህ ጀግኖች የሰው ልጆች ላይ የዘመተውን ይህን ጠላት ለመመከት ከፊት ተሰልፈው ዋጋ እየከፈሉ ይገኛሉ ለዚህ ከፍ ያለ ስራቸውም የከበረ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

እኛም የኛ መጠንቀቅ እምንዎዳቸውን ከመጠበቅ አልፎ ለእኛ ሲሉ በደጅ ላሉ ሁሉ ጥንቃቄ ነውና በምንችለው አቅም እየተጠነቀቅን እኛም በዚህ ሀገራችንን እንድንጠቅም ይሁን በማለት መለከታችንን እናስተላልፋለን።

ቸር ያሰማን!

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ኬላ

ሕግ

# ተጠንቀቅ!

ጥበቡ ኃ.

## ጤና ይስጥልኝ!

መቼም የጤና ዋጋ ለሁላችንም በዘመነ-ኮሮና ቁልጭ ብሎ የተገለጠልን ይመስለኛል፡፡ የጤና ገንዘብነቱ እንዲህ ውድ መሆኑን በበኩሌ እንደዚህ ወቅት ዘልቆ የገባኝ አይመስለኝም፡፡ ለአፍታ በዚህ ክፉ ተህዋሲ ተለክፈው በሰው-ሰራሽ መተንፈሻ መሳሪያ እጅ ስር ያሉትን ሳስባቸው፤ ለመግለጽ በሚያስቸግር ሁኔታ እደነግጣለሁ፡፡ ለምን ያህል ሳምንት፣ ቀናት፣ ሰዓት ወይ ደቂቃ እቋቋመው ይሆን የሚለውን ሳስበው ውጤቱ ያሳስበኛል፡፡ "በዚያ ላይ ቀጭን ነኝ!" አለ ገጣሚው ሃሃሃ

ለሁሉም ይኽ ጊዜ እስኪያልፍ "ውሃን ከቀለብ ጤናን ከገንዘብ" ቆጥራችሁ በያላችሁበት ሰላማችሁ በዝቶ እንድትኖሩ መልካም ምኞቴን ገልጬ ወደ ጉዳዩ መግባት ወድጃለሁ፡፡

ዛሬም እንደተለመደው ከሐገሪቱ ሕግ ወ ፖለቲካ ከባቢ አንዱን ርዕስ መርጬ ስለ ‹ሰብዓዊ መብቶች› ላወጋችሁ ነው፡፡ ተቀማጭነቱን እንግሊዝ ያደረገው ‹አምነስቲ ኢንተርናሽናል› የተሰኘ ዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ድርጅት ሰሞኑን ኢትዮጵያን አስመልክቶ እጅግ አነጋጋሪ ባለ 50 ገጽ የሐገሪቱን ሰብዓዊ መብቶች አያያዝ የሚዳስስ መግለጫ አውጥቷል፡፡ ከድህረ-መጋቢት/2010 ወዲህ ኢትዮጵያ እዲህ መረር ባለ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስትከሰስ ካልተሳሳትኩ የመጀመሪያዋ ነው፡፡

በእኔ እይታ መግለጫው በዚህ ልክ አነጋጋሪ ሆኖ የሰነበተው በሁለት ዐብይ ጉዳዮች መነሻነት ይመስለኛል፡፡ አንደኛው ከ 2010ሔ ለውጥ በኋላ የሐገሬው ሕዝብ ፖለቲካዊ ንቃት እና ተሳትፎ እጅጉን ከፍ ያለ መሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው በሪፖርቱ ውስጥ ተፈጽመዋል ተብለው የተዘረዘሩት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እጅግ ዘግናኝ እና አስፈሪ በመሆናቸው ነው፡፡ በእርግጥ ለየራሳቸው ፖለቲካዊ ትርፍ መግለጫውን ያጣጣሉትም፤ ያጯጯኁትም መኖራቸውን ዘንግቼው አይደለም፡፡ የምንመኛት ኢትዮጵያ በገቢር እውን እንድትሆን ከፈለግን መሰል የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ከፖለቲካው በመነጠል (depo-liticize) መፍትሔያቸው ላይ ብንማስን ይሻላል ብዬ ስለማምን ነው፡፡ (በሌላ እርግጥ) የችግሩ አንዱ (ምናልባትም ዋነኛው) መንስዔ የሐገራችን ፖለቲካ ‹ንቅዘት› መሆኑም አልጠፋኝም፤ ፖለቲካውን መፍትሔ ለማድረግ አስበን የሞከርናቸው ሙከራዎች ሁሉ ጨንግፈው ስላየሁ እንጂ!

ወደ ሰሞነኛው የኢትዮጵያ ሁኔታ ከመመለሴ በፊት የ ‹ሰብዓዊ መብቶች› ስረ-ነገርን አስመልክቼ ትንሽ ብል ጥሩ መነሻ ይሆነናል፡፡ ሰብዓዊ መብት ቀዳማዊ መሰረቱን ከግሪክ ፍልስምና እና ልዩ ልዩ የዓለም ኃይማኖቶች እሳቤ ቀድቶ ሲጀምር የ18ኛው ክ/ዘመን የ‹አብርሆት› ንቅናቄ ግን ጽንሰ-ሀሳቡን አፋፋው ሊባል ይችላል፡፡ ሰብዓዊ መብት፣ የሰው ልጅ በረዥም ዓመታት የሕይወት ጉዞው ካሳለፋቸው የእርስ በእርስ ግንኙነቶች እየተማረ ለሰብዓዊ ልዕልና እና ነጻነት ያለውን እይታ እያዳበረ ሲመጣ ቅርጽ የያዘ ሀሳብ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በተለይም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የሰው ልጅ ያለፈባቸው እጅግ የከፉ ሰብዓዊ ቀውሶች በዚህ ጉዳይ ላይ መሬት የረገጠ ሀሳብ ሊኖር እንደሚገባ ያስተማሩ ክስተቶች ነበሩ፡፡ ሐገራት ዜጎቻቸውን ለማስተዳደር የሚጠቀሙበትን የ‹እኔ አውቅልሀለው› እና ኋላቀር አያያዝ ቀርቶ አዲስ በሚፈጠረው የዓለም ስርዓት ውስጥ በሚቀመጠው ጠቅላላ ገዢ መስመር መሠረት መሆን እንደሚገባው ከስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡

በዚህ የጋራ ስምምነት መነሻነት በ1950ዎቹ በተባበሩት የዓለም መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) ስር ዓለም-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ፣ ዓለም-አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች ቃልኪዳን፣ ዓለም-አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ቃልኪዳን ስምምነቶች እንዲዘጋጁ ሆኗል፡፡ እነዚህ ሦስቱ ሰነዶች በጥቅሉ ዓለም-አቀፉን የሰብዓዊ መብቶች የሕግ ሰነድ (International Bill of Rights) ይባላሉ፡፡ እያንዳንዱ አባል ሐገራት በእነዚህ ሰነዶች ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች፡- አንደኛ የማክበር (Respect)፡- ራሳቸው መንግስታት ከመጣስ ሊቆጠቡ ይገባል የሚል፣ ሁለተኛ የመጠበቅ (Protect)፡- ሌሎች አካላት የዜጎችን መብቶች እንዳይጥሱ የመከላከል፤ እና ሦስተኛ የማሟላት (Fulfill)፡- ዜጎች በመብቶቻቸው የሚጠቀሙበትን አስቻይ ሁኔታ የማሟላት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

በርግጥ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የሰብዓዊ መብቶች ግዴታዎችን በአቀባታዊ ግንኙነት (Vertical Relationship) ለመንግሥታት ብቻ የሚሰጡት እዳ አይደለም፡፡ ይልቁንስ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተወናዮችን እና አካላት እንዲሁም በጎንዮሽ ግንኙነት የሚገኙት ግለሰቦችም መሰል ግዴታ እንደሚኖርባቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህ ሲባል ግን መንግሥታት ሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ የሚኖራቸው ድርሻ ከፍ ያለ፣ ግዴታቸውም ከሌሎች የተለየ መሆኑን አያስቀረውም፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ ሐገራት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያጋልጡ መግለጫዎችን በሰሙ ጊዜ ጣት መቀሰር፣ ድርጅቶቹን ማሸማቀቅ፣ የተባሉትን

ኹነቶች ማጣጣል እንጂ፤ እውነትነታቸውን ማረጋገጥ፣ አጥፊ አካላት ላይ እርምጃ መውሰድ፣ ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ መጣር የሚባሉትን ሥራዎች አይደፍሯቸውም፡፡ ከሰሞኑ በሐገራችንም የታየው ይኸው ነው! በመግለጫው እንደተካተተው መግለጫው ይፋ ከመደረጉ ሳምንታት በፊት የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ምላሽ እንዲሰጡበት ቢጠየቁም፤ ከአንድ ተቋም ውጪ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡ አሁን ነገሩ በሚዲያ ይፋ ሲሆን ደግሞ በየፊናቸው መግለጫውን በማጣጣል ተጠምደዋል፡፡

በእኔ እምነት አምነስቲ ኢንተርናሽል ያወጣው መግለጫ ከነድክመቱ የሐገሪቱን የሰብዓዊ መብቶች አሁናዊ ገጽታ በደንብ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ በሌሎችም ዓለማት እንደታየው በእኛም ሐገር ባለፉት ጊዜያት እንደታዘብነው የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ ሲከፋ፤ መንግሥታት ይናወጣሉ፣ ዜጎች አልገዛም ይላሉ፣ ሐገር ትንገዳገዳለች፡፡ ባስ ሲልም ትፈርሳለች፡፡ እነ ሶሪያ ከተኙበት ሲነቁ ሐገር አልባ ያደረጋቸው መነሻ ሰበብ የአል-አሳድ መንግሥት ሲያደርስ በነበረው ግፍ የተማረሩ የሐገሬው ሰዎች አደባባይ ወጥተው ከመንግሥት ጋር በገጠሙት እንካ-ሰላምትያ መግፍዔነት ነው፡፡

ከሰሞኑ በብዙኃን መገናኛ ብሎም በየማኅበራዊ ሚዲያው የታዘብነው ውይይት አንድ ነገር አስረግጦ መናገር የሚችል ይመስለኛል፡፡ ይኸውም፡- መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች እና ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን ካለመወጣቱም በላይ ራሱም ስጋት እየሆነ መምጣቱን ነው፡፡ ባለፉት ጊዜያት ተስፋ የሚሰጡ የተቋማት እና የሕግ ማሻሻል ጅምሮች ቢኖሩም፤ የተሰሩትን መልካም ሥራዎች በዜሮ የሚያጣፉ ሥራዎችም መሠራታቸው አልቀረም፡፡ አሁን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሁኔታችን አስጊ ደረጃ ላይ ለመድረሱ በቂ ምልክቶች ታይተዋል፡፡ እናም ጠንቀቅ እንበል፣ ሽርተት ካልን ወደነበርንበት አዙሪት መመለሳችን ነው፡፡

…//…

‘‘የምንመኛት ኢትዮጵያ በገቢር እውን እንድትሆን ከፈለግን መሰል የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ከፖለቲካው በመነጠል (depoliticize) መፍትሔያቸው ላይ ብንማስን ያሻካል ብዬ ስለማምን ነው፡፡’’

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ቀለም

# ህገ ወጥ እስራትና አሁናዊ እውነታዎች

## ህገወጥ እስራት?

ህገ ወጥ እስራት ማለት አንድን ሰው ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን ህግ ከሚፈቅደው አግባብ ውጪ በቁጥጥር ስር በማዋል እንደፈለገው እንዳይንቀሳቀስ አድርጎ በአንድ ቦታ ወይም ቤት ውስጥ ማቆየት ማለት ነው[1]፡፡

ህገወጥ እስራም የሚከለክሉ ህጎችና የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 17/02/ ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ስርአት ውጭ ሊያዝ እንደማይገባ ይደነግጋል እንዲሁም ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የአፍሪካ የሰዎችና ህዝቦች መብት ቻርተር አንቀጽ 2 ሰዎች ሁሉ ሁሉንም መብቶች ያለ ምንም አድልኦ የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 9(1) እያንዳንዱ ሰው የግል ነፃነትና ደህንነት መብት እንዳለው በማረጋገጥ ማንም ሰው ከህግ ውጭ አይያዝም፣ አይታሰርም፣ በወንጀል የተጠረጠረ ሰውም ቢሆን ፍርድ ቤት ቀርቦ ዳኝነት የማግኘት፣ ይህ ሳይሆን ቢቀር ደግሞ የመለቀቅ መብት እንዳለው የዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 3 በግልፅ ይደነግጋል፡፡

ከላይ የተገለፁትም መብቶች የማክበር ግዴታ የማን ነው የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የማክበር ብቻ ሳይሆን የመጠበቅ፣ የማሟላትና የማስተዋወቅ ግዴታ የተጣለው በዋናነት በመንግስት ላይ ነው ይሁንና ሌሎች አካላትም የሰዎችን መብቶች የማክበር ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት እየተፈፀሙ ያሉ ህገ ወጥ እስራቶች በአገራችን በዚህ ግዜያት እንዱሁም በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ህገ ወጥ እስራቶች በመፈፀም ላይ ይገኛሉ በዋናነትም በተለይም መንግሥት የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) በኢትዮጵያ ሊያደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ ለመቆጣጠርና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በማሰብ ሚያዝያ 2 ቀን 2012 ዓ.ም 2 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ካወጣበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ዜጎች ይህንን አዋጅ ጥሳችኋል በማለት ታስረዋል አሁንም እየታሰሩ ይገኛል፡፡

### ለአብነት ያክልም፡-

- በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ በርካታ ሰዎች "ለኦነግ ሸኔ ድጋፍ ትሰጣላችሁ" በማለት የኢሰመጉ የቀጠናው ፅ/ቤት የኮሚቴ አባል ጭምር ያለ በቂ ምክንያት ታስረዋል፡፡ በዚህ አካባቢ አሁንም የሚታሰሩ ሰዎች ቁጥር በመጨመር ላይ ይገኛል፣

- በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም ጎንደር ከተማ "ከህገወጥ ፋኖዎች ጋር ግንኙነት አላችሁ" በማለት ሰዎች እንደሚታሰሩ፣ በባህር ዳር ከተማ ከ200 በላይ የሚሆኑ ባጃጆች "በህገወጥ መልኩ ነው ታርጋ ያወጣችሁት፣ ህገወጥ መሳሪያ ታዘዋውራላችሁ፣ ሰው ታግታላችሁ" ተብለው ታስሮባቸዋል በተጨማሪም ከሰኔ 15 የክልል ባለስልጣነት ግድያ ጋር በተያያዘ የታሰሩ ሰዎች በማረሚያ ቤት ብቻ እንዲቆዩ መደረጉ፣

- በደቡብ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ የፖለቲካ ተፎካካሪ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ በተለያዩ ጊዜያት ህገወጥ እስራቶች ተፈፅመዋል አንዳልዶቹም ለቀናት ከታሰሩ በኋላ መፈታታቸውን ተሰምቷል፣

- በሶማሌ ክልል የክልሉ የምክር ቤት አባላት ለዕስር የተዳረጉበት ጉዳይ ግልፅ ካለመሆኑም በተጨማሪ የህግ ባለሙያ ሳያገኙ እንዲሁም መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው ባልተሟላ ሁኔታ ታስረው እንደሚገኙ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየሰማን ነው፣

- በአዲስ አበባም የፓርቲ አመራሮችና አባላት በተለያዩ ጊዜያት ያላግባብ ታስረው እየተፈቱ ይገኛል በተጨማሪም ማስክ አላደረጋችሁም በማለት ቁጥራቸው በርካታ የሚሆኑ ሰዎች መታሰር ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፣ ምክንያቱም እነዚህን ሰዎች በአንድ ላይ ሰብስቦ ከማሰር ይልቅ አስተምሮ መልቀቅ የተሻለ ውጤት ያመጣል በተለይም መንግስት የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመቀነስ እስረኞችን እየፈታበት ባለበት ሁኔታ ማስክ አላደረጋችሁም በማለት ተጨማሪ ሰዎችን ማሰር ተገቢ አይደለም፡፡

በሌሎችም ክልሎችና አካባቢዎች ተመሳሳይ ህገወጥ እስራቶች ተፈፅመዋል በመፈፀምም ላይ ይገኛል፡፡

1

1 1 https://legal-dictionary.thefreedictionary.com

2 የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ቁጥር 3/2012

# መንግስት ሊያደርገው የሚገባቸው አበይት ስራዎች

ህገወጥ እስሮች እንዳይፈፀሙ መከላከል ከሚቻልባቸው በርካታ እርምጃዎች ውስጥ የፖሊስና የፍትህ ተቋማትን አቅም ማጠናከርና እንዲሁም የፖሊሶችን የህግና የሰብዓዊ መብቶችን እውቀትና ግንዛቤ በየጊዜው ማሳደግ ይገኙበታል ስለሆነም መንግስት የፍትህና የህግ ተቋማትን በቂ ትኩረት በመስጠት ማጠናቀር ይኖርበታል፡፡

የዜጎችንም መብት የሚጥሲ አካላት ሁሉ በህግ አግባብ ላጠፉት ጥፋት ተጠያቂ መሆን ይኖርባቸዋል በዚህም ረገድ መንግስት ቁርጠኛነቱን በተግባር ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ይህ ሲሆን የዜጎግ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የበለጠ ይከበራሉ፡፡

## ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶችና እንዲሁም በአገራችን የበላይ ህግ እውቅና ያገኙት መሰረታዊ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚሸራረፉበትና ጭራሹንም በሚጣሱበት ሁኔታ የህዝብን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ እየተባሉ የሚወጡ ህጎች የታለመላቸውን ግብ ከመምታት ይልቅ በህግ ሽፋን ለሚፈፀም ህገወጥ እስራቶች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ስለሆነም መንግስትና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በቂ ትኩረት በመስጠት ለዜጎች መብት መከበር ሊሰሩ ይገባል፡፡

ቸር ያሰማን!

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።